# ኢትዮጵያ አትመችም

# በደም ግብር ለሚነግሥ

በላእከ ጥበባት ፍጹም ተድላ /ካናዳ

ለህዝባችን ሰላም ብንመኝ ይሻላል

ሁዋላ እንዳይ ሆንብን የብብትን መጣል

የትምክህት ስካር ለሷስ ምን ጠቀማት

ከጥንት እስከ ዛሬ ስትደማ የምናያት፤

ጥላቻና ትምክህት አጉል ጽንፈኝነት

አንዱ በአንዱ ላይ እምነት በማሳጣት

ንጹህ ደም አፍስሶ ወደ ሥልጣን መዉጣት

ስንቶች ተዋረዱ ተጠቅመዉ የሷስልት፤

በጥንቆላ ተመስረታ

የሰዉ ፍጡር አለ ፍላጎቱ በቁጥጥር ስር አስገብታ

በኒምሮድ ረድአ መስቴማ በሃዳኒነቷ የታወቀች

የምስጢር ሃማኖት ወይንም ባቢሎን የተባለች

የመርዝ ቅጠሏ አስፍታ

ግብጥ፤ ተሰሎንቄ፤ ሮም፤ እንግልጣርን የመረዘች

አቅማረ ህላውየ ቀምራ ዓውደ አዋርህ አበጅታ

በሷ ቀመር ሊወሰን የሰዉ ፍጡር እጣፈንታ

ተንኮታኮተች ላትንሳ ስንቱን ፍጡር አፋጅታ።

ክብርና ምስጋና ለአበዉ

በዓይነ ህሊና ተመልክተዉ በእግረ ልቦና ተጉዘው

አማልክተ ግብፅ ወባቢሎን አኮ አማልክተ ኢትዮጵያ ብለዉ

ጥንቆላና መተትን የሪእካርኔሺን አንድምታን ኮንነዉ

እዉነትና የእዉነት አምላክ ዘልአለማዊነት አምነዉ

እውነት ቅጠሏ የማይጠወልግ እንደ ተተከለች ዛፍ በዉሃዳር

በሽማግሌ በጋዳ የምትዳኝ፤ የምትጠበቅ በህገ አምላክ ወታደር

አወረሱን እጆችዋን ወደ ፍቅር አምላክ የምትዘረጋ ሃገር፤

ከእስራኤል፤ ከሮም፤ ከቐርሺ፤ ከአፆኪያ

የአንድ አምላክ ህዝቦች ሲበዛባችዉ ግድያ

እግራቸዉን አጥባ ያላትን አቅርባ የሆነቻቸዉ መጠግያ

ኢትዮጵያ ነበረች

ከፈጣሪዋ ፍጹምነት፤ቅንነት፤ ርህራሄ የተቸረች፤

ሰይፍህ ከሰገባህ አምልህ ከጉያህ

ለትዉልድ ብላ ሃብተ ትእግስትን ያወረሰች፤

አዎን ብዙ መከራ አሳልፋ

በልጆችዋ መስዋእትነት ጨለማዉን ሥርዓት አሸንፋ

ህዝቦችዋም ተፈቃቅደዉ

ማንም እኔ ነኝ የበላይ ሳይላቸዉ

ደምቀዉ ተዉበዉ ባንድነት

ባንድ ድምፅ አጽድቀዉ ሕገ መንግስት

ተበስሮ በምድራችን የህዳሴ ዘመን ብስራት፤

ብለዉ ተነሱ ድህነት ነዉ ጠላታችን

ሃገርን ለማልማት እንገድብ አባይን

አንድ እንደ ሺ ሆኖ ፤ሺም እንደ አንድ ሲሆን

የሃገር ገጽታ ተለዉጦ ዉጤቱም  እያየ ዓይናችን

በዚህ በዲያስፖራ

ባንድ ቃል ተነስተን ታሪክ እንዳንሰራ

ኢህአዴግ አውግዞ

ኩፖን እንዳትገዙ እያሉ  የሚጮሁ በፀሓይ ጠራራ

ቅጥፈት ተምላሳቸዉ ተጃቸዉ ባንዴራ፤

ልብ በይ ልብ በል ያገር ልጅ ወገኔ

ጠላት ድልድይ አይስራ ብእኛዉ ይሉኝታ በእኛዉ ምናኔ፤

ማይረባ ያገር ልጅ አብሮህ አይሰደድ

ያገር አሰዳቢ ታመን ሲሉት ሚከድ

በንፁሃን ልብ የቡሃቃ

 የቂም በቀል  እርሾ መጨመር የሚወድ

አገር ሰላም ሳለ ናፋቂ ጦር አዉርድ

እንደ ኒምሮድ እንደ ሰሜራምስ

መሆን ከመርጡ የመስቴማ ፈረስ

ዘቦ እዝን ሰሚአ ለይስማእ (ጆሮ ያልዉ ይስማ)

ዉጤቱ አይቅሬ ነዉ ወድቆ  መፈራከስ

ተንግዲህ ኢትዮጵያ  ፈጽማ አትመችም  በደም ግብር ለሚነግሥ።